# የባሃኢ ሃይማኖት
# አጭር መግለጫ

2ኛ ዕትም

መስከረም 2009

## የባሃኢ ሃይማኖት ዓላማ

የባሃኢ እምነት ክርስትናን እና እስልምናን ከመሳሰሉ ዋና ዋና ዓለም አቀፋዊ ሃይማኖቶች አንዱ ነው። የራሱ ቅዱሳን መጽሐፍት እና ህግጋት ያሉት ራሱን የቻለ እምነት ነው። የባሃኢ ሃይማኖት ተቀዳሚ ዓላማ ሁሉንም ዘሮችና ሕዝቦች በአንድ ሁሉን አቀፍ እቅድና እምነት ማዋሃድ ነው። የባሃኢ ሃይማኖት ተከታዮች ባሃኢዎች ይባላሉ። የሃይማኖቱም መልዕክተኛ የሆነው የአምላክ ግልጸት ባሃኦላህ ይባላል። ባሃኦላህም እንደሚከሰት በሁሉም ሃይማኖቶች ትንቢት የተሰጠለት ነው። እንደሚታወቀው ሁሉም ሃይማኖት በምድር ላይ ሰላምና ስምምነት የሚመሰረትበትና የሰው ዘርም በብልጽግናና በፍስሃ የሚኖርበት ዘመን እንዲሚመጣ ተስፋ ሰጥተዋል። ባሃኦላህ እርሱ ይህንን ትንቢት ይፈፅም ዘንድ ከእግዚአብሔር የተላከ ነቢይ እና መልዕክተኛ እንደሆነ አስተምሯል። ባሃኢ ማለት የባሃኦላህ ተከታይ ማለት ነው። ባሃኢዎች የዘመናትና የሕዝቦች ሁሉ ተስፋ የሆነው ትንቢት ይሟላና በምድር ላይ የአንድነትና የሰላም ዘመን ይመሠረት ዘንድ የሚያስችሉትን በባሃኦላህ የተገለፁ ትምህርቶችንና ህግጋትን ያምናሉ፤ በግል ሕይወታቸውና በምድር ላይም ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ ይተጋሉ።

ከቅዱሳን ጽሑፎቹ በአንዱ ባሃኦላህ እንዲህ ይላል፡-

*"ጌታ ከፍተኛ ፈውስና እጅግ በጣም ታላቅ መሣሪያ አድርጎ ለመላው ዓለም መፈወሻ ያዘዘው የሕዝቦችዋን በአንድ አለማቀፋዊ ዓላማ፣ በአንድ የጋራ እምነት ሥር ማሰባሰብን ነው።"*

## ከባሃኦላህ ትምህርቶች ጥቂቶቹ

### የእግዚአብሔር አንድነት

የፍጡራን ሁሉ ፈጣሪና ጌታ የሆነ አንድ አምላክ እንዳለ፣ የአምላክ ሕላዌ ግን በሰው ልቦና የማይደረስበት እንደሆነ ባሃኦላህ ያስተምረናል። ይህ ማለት ስለአምላክ በአእምሮአችን የምንቀርጸው ነገር የአምላክን ሕላዌ ወይም እውነተኛ ምንነት

በምልዕነት አያስጨብጠንም ማለት ነው። በአጠቃላይ መልኩ ስናየው፣ ልክ ወንበር አናጺውን ሊገነዘብ እንደማይችል ሁሉ፣ የተፈጠረ ነገር ሁሉ ስለፈጣሪው በምልዐት ሊገነዘብ አይችልም። አምላክ የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ ነው። መላውን ምድር ከነፍጥረቷ፣ ሕዋን ከነፈለኮቿ ፈጥሯል። አምላክ ፍጥረትን ካለመኖር ወደመኖር ያመጣው ለፍጡራኑ ባለው ፍቅር ምክንያት መሆኑን፣ የፍጥረት ሕልውናም ከአምላክ ፍቅር መገለጫዎች አንዱ እንደሆነ፣ ባሃኦላህ ያስተምረናል ።

በባሃኦላህ አማካኝነት የተገለፀው ቃለእግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡-

*የሰው ልጅ ሆይ!*
*ያንተን መፈጠር ወደድሁ፣ ስለዚህም ፈጠርሁህ። ስለዚህም ስምህን እንዳነሳና ነፍስህን በህይወት እስትንፋስ እሞላት ዘንድ አንተም አፍቅረኝ።*

ስለዚህ ምንም እንኳ የአምላክ ሕላዌ ከግንዛቤያችን የላቀ ቢሆንም ፍቅሩ ሕይወታችንንና ሕልውናችንን ሳያቋርጥ ይዳስሳል። ይህ ፍቅርም ወደ እኛም የሚደርሰው በቃልኪዳኑ አማካኝነት ነው። በዚህ ዘለዓለማዊ ቃልኪዳን መሠረት አምላክ ብቻችንን ያለመመሪያ ፈጽሞ አይተወንም። የሰው ልጅ ከእርሱ በራቀ ቁጥር በመልዕክተኛው አማካኝነት ይገለጽና ፍቃዱንና ዓላማውን ያሳውቀናል። መገለጽ ወይንም ግልጸት ማለት ከዚህ ቀደም የማይታወቅን ነገር ማሳወቅ ማለት ነው።

የአምላክ ግልጸቶች የአምላክን ቃልና ፍቃድ ለሰው ልጅ የሚገልጹ ሰብዕናዎች ናቸው። በየዘመኑ የአምላክን ፈቃድ (ሃይማኖት) የሚገልጹ መልዕክተኞቹ ከዚህ በተጨማሪ በሌሎች ስሞችም ይጠራሉ፡ ክስተት፣ ወይም ነቢይ፣ ወይም መልዕክተኛም ይባላሉ። እነዚህን የአምላክ ግልጸቶች ካዳመጥን አምላክን አዳመጥን ማለት ነው። አምላክ እነዚህን መልዕክተኞቹን ሊታወስ ከማይችል ጊዜ ጀምሮ ለፍጡሮቹ ሲልክ ነበር። ወደፊትም መላኩን አያቋርጥም። ታሪክ ከሚያስታውሳቸው የአምላክ ግልጸቶች መካከል አብርሃም፣ ሙሴ፣ ኢየሱስ፣ እና ነብዩ መሐመድ ይገኙበታል። ለዚህ ዘመን ከአምላክ የተላኩት ግልጸቶች ደግሞ ባብ እና ባሃኦላህ ናቸው።

ከላይ እንደተባለው አምላክን በቀጥታ ልንደርሰበት አንችልም። እነኝህ ፍጹም የሆኑ ሰብዕናዎች ግን በየዘመኑ ወደ እኛ ይላካሉ። በመካከላችን ይኖራሉ። መመሪያ ይሰጡናል። ቁሳዊና መንፈሳዊ ዕድገትን (መዳንን) ለመቀዳጀት በሚያስችለን ኃይል (በመንፈስቅዱስ ሃይል) ይሞሉናል።

ስለዚህ የባሃኦላህ ትምህርቶች ከሌሎች የአምላክ ሃይማኖት ትምህርቶች ጋር ይስማማሉ። ትምህርቶቹም ለዘመናችን የሰው ልጅ ሁኔታ መፍትሄ የሚሆኑ ናቸው። የሰውን ልጅ ሁኔታ ብናጤነው ሌላ የአምላክ ግልጸት መምጣት ያለበት ትክክለኛው

ጊዜ አሁን መሆኑን እንስማማለን። ስለምንኖርበት ዘመን ሁኔታ ከሚናገሩ የባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ የሚከተለውን እናገኛለን፡

*“ይህ ቀን፣ የእግዚአብሔር እጅግ በጣም የላቁ ችሮታዎች በሰዎች ላይ የፈሰሱበት፣ የእርሱ እጅግ በጣም ታላቅ ፀጋ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ውስጥ የተናኙበት ቀን ነው። የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ልዩነቶቻቸውን በማስወገድ፣ በእርሱ እንክብካቤና ፍቅራዊ ደግነት ዛፍ ጥላ ሥር፣ በፍጽም አንድነትና ሰላም መኖር አለባቸው።”*

## የሰው ዘር አንድነት

የባሃኦላህ መገለጽ ተቀዳሚ ዓላማ የሰው ዘር አንድነትን መመሥረት ነው። እኛ ሁላችንም የአንደ ዛፍ ፍሬዎችና የአንድ ቅርንጫፍ ቅጠሎች መሆናችንን የባሃኦላህ ትምህርቶች ይነግሩናል። ምንም እንኳን የተለያየ ዘር፣ ቀለምና አገር ቢኖረንም፣ ምንም እንኳን የተለያየ የአኗኗር ሁኔታና ደረጃ ቢኖረንም ስረመሠረታችን ግን አንድ ነው።

በባሃኦላህ አንደበት እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡-

*“የሰው ልጅ ሆይ!*

*... ለምን ከአንድ ዓይነት ትብያ እንደፈጠርናችሁ ኢታውቁምን? አንዱ ከሌላው ራሱን ከፍ እንዳያደርግ ነው። እንዴት እንደተፈጠራችሁ በልባችሁ ዘወትር አሰላስሉ። ሁላችሁንም ከአነድ ኢይነት ነገር ስለፈጠርናችሁ፣ ከውስጣዊው ሕልውናችሁ በምግባራችሁና በሥራችሁ፣ የአንድነት ምልክቶችና ከዓለማዊ ነገሮች የመላቀቅ ሕልውና ይገ ለጽ ዘንድ፣ ልክ እንደ አንድ ነፍስ፣ በአንድ እግር የመራመድ፣ በአንድ አፍ የመብላትና በአንድ ምድር የመኖር፣ ግዴታ አለባችሁ።”*

የሰው ዘር በአንድ ሰፊ የአትክልት ስፍራ ሊመሰል ይችላል። በዚህ አትክልት ቦታ የተለያዩ ቅርጾች ቀለሞችና መዓዛዎች ያላቸው አበባዎች ጐን ለጐን ያድጋሉ። የአትክልት ሥፍራዉ ውበት የአበቦች የተለያየ ቀለማት ቅርጽና መዓዛ ውጤት ነው። ልክ እንደዚሁ በአካላዊ አቋማችን፣ በባሕሪያችን፣ ከተለያዩ ማህበረሰቦችና ሃይማኖቶች በመምጣታችን፣ በአስተሳሰቦቻችንና በአመለካከታችን መካከል ያሉት ልዩነቶች ግጭትንና ጥልን እንዲያመጡ መፍቀድ የለብንም። የተለያዩ አበቦች ውበትን እንደሚገልጹ ሁሉ እኛም ልዩ ልዩ መሆናችን የውበታችን መገለጫ መሆን አለበት።

የሰው ዘርን ሁሉ በአትክልት ቦታ እንደሚበቅሉ ውብ አበቦች አድርገን ማየት አለብን። የዚህ አትክልት ቦታ አበቦች በመሆናችንም መደሰት አለብን። ምንም እንኳን የሰው ዘር አንድነት የማይታበል ሐቅ ቢሆንም በምድር ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች ከአንድነት እጅግ የራቁ ከመሆናቸው የተነሳ እነርሱን አንድ ማድረግ ቀላል ሥራ አይደለም።

አንድ ሰው የባሃኢ ማህበረሰብን ለመቀላቀል ሲወስን እኛ ባሃኢዎች አንድነትን ለመገንባትና ዘለቄታ እንዲኖረውም ለማድረግ በምናደርገው ጥረት ተሳታፊ ይሆናል። የጦርነት ሃሳብ ሲመጣ ወዲያውኑ በሰላም ሃሳብ እንድንተካው የባሃኢ እምነት ያስተምረናል። በልባችን ውስጥ የጥላቻ ስሜት ሲቀሰቀስ ወዲያውኑ በፍቅር ስሜት መተካት አለብን። ከከንቱ ጥላቻ ነፃ ለመሆን የተቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን።

የተሻለ ዓለምን ለመገንባት ከፍተኛ መሰናክል ከሆኑት መካከል የዘር፣ የቀለም፣ የብሔር፣ የባህል፣ የሃይማኖትና የጾታ ከንቱ ጥላቻዎች ይገኙበታል። በአንድነት ጐዳና እንዴት መጓዝ እንደምንችልና ሌሎችም ይህንኑ መንገድ እንዲከተሉ እንዴት መርዳት እንደምንችል የባሃኢ ጽሑፎች ያስተምሩናል። ከባሃኢ ቅዱሳት ጽሑፎች የተወሰደ አንድ ድንቅ ምንባብ አለ። እንዲህ ይላል፦

> *"ባሃኦላህ የአንድነትን ማዕከል ፈጥሮአል። ሕዝቦችን ሁሉ አንድ ለማድረግና በሁሉን ዓቀፍ ውሕደት ድንኳን ጥላ ሥር ... ሁሉንም ለመሰብሰብ ንድፍ አውጥቶአል። ይህ የመለኮታዊው ቸርነት ሥራ ነው። የአንድነት እውንነት በመሐከላችን እስኪኖርም ድረስ በሙሉ ልብ መጣር አለብን። ይህን ስንተገብርም ጥንካሬ ይሠጠናል።"*

## የባሃኢ እምነት አጭር ታሪክ

ባሃኦላህ በኢራን ዋና ከተማ በቴህራን እ.ኤ.አ በ1817 ተወለደ። ከልጅነቱ ጀምሮ የታላቅነት ምልክቶች ይታዩበት ነበር። ትምህርት ቤት መግባት አላስፈለገውም ነበር። ምክንያቱም አምላክ መለኮታዊ ዕውቀት አጐናጽፎታልና። ባሃኦላህ ታላቅና ታዋቂ ከሆነ ቤተሰብ ነበር የተወለደው። ወጣት በነበረበት ጊዜ ንጉሱ ከፍተኛ ሹመት ሰጥቶት ነበር። እርሱ ግን አልተቀበለውም። ጊዜውን የተጨቆኑትን፣ ሕሙማንና ድሆችን በመርዳት እንዲሁም ፍትህን በማራማድ ሊያውለው ፈለገ።

የባሃኦላህ መከራ የጀመረው ወዲያው የአምላክን እምነት ለማወጅ እንደተነሳ ነበር። ሕይወቱን ሁሉ የኖረው በግዞት፣ በእስራትና በጭቆና ነበር። መጀመሪያ በቴህራን ከተማ አንድ ጨለማና ፀሐይ የማይደርስበት ጉርጓድ ውስጥ በሠንሰለት ታሰረ። ከዚያም ከአንዱ አገር ወደ ሌላው አገር አራት ጊዜ በግዞት ተንከራተተ። በመጨረሻም በዚያ

ዘመን በኦቶማን ግዛት ውስጥ የእስር ከተማ ወደነበረች በእስራኤል አገር ወዳለችው አቆር ከተማ ተጋዘ። በዚች ከተማ ስቃዩ ከሙብዛቱ የተነሳ አቆርን *እጅግ በጣም ታላቁ እስር ቤት* ብሎ ጠራት። ከጽሑፎቹ በአንዱ ይህን እናነባለን፡-

> *"... በዚህ ሩቅ ወህኒ ቤትም ስቃዬን ግዞቴን አስታውስ፣ እንዲሁም የጠላቶች ሰይፎች ጭፍጨፋ ቢያዘንቡብህም ልብህ እንዳያመነታ በፍቅሬ የፀናህ ሁን።"*

ሁለቱ ኃያላን መንግስታት፤ ማለትም የኢራን ንጉሥና የኦቶማን ንጉሠነገሥት፣ ባሃኡላህንና ትምህርቶቹን ለመቃወም ከፍተኛ ጥረት አደረጉ። ነገር ግን የእውነት ብርሃን በቀላሉ የሚጠፋ አይደለም። ይህን እንደእሳት የሆነውን እውነታ ለማጥፋት በላዩ ላይ የሚደፋው ውሃ ወደ ነዳጅነት ተለውጦ የበለጠ እሳቱን አፋፋመው። እያደገ የሄደውን የባሃኡላህን ታዋቂነት ለማቆም ምንም ማድረግ አልተቻለም። ባለስልጣኖቹ የበለጠ ሩቅ ቦታ ባጋዙት ቁጥር ወደ ትምህርቶቹ የሚሳቡና ብርታቱንና ግርማውን የሚያውቁ ሰዎች ቁጥር እየበዛ ሄደ።

የማያቋርጥ ጭቆና ቢደርስበትም ከአርባ ዓመታት ለበለጠ ጊዜ ባሃኡላህ የእግዚአብሔርን ቃል መግለጽን ቀጠለ። ወደ እዚህ ዓለምም እጅግ በጣም ከፍተኛ ፍቅርና መንፈሳዊ ኃይል ከማምጣቱ የተነሳ የእምነቱ ድል የተረጋገጠ ሆኗል። እ.ኤ.አ 1892 ባሃኡላህ ከዚህ ዓለም ተለየ። ባሃኢዎች በምድር ላይ እጅግ በጣም ቅዱስ ቦታ ነው የምንለው መካነ መቃብሩ እስራኤል አገር በአቆር ከተማ አቅራቢያ ይገኛል። ባሃኡላህ ስለደረሰበት መከራ እንደሚከተለው ጽፏል፡-

> *"... የሰው ልጅ ከእስረኝነት ነፃ ይወጣ ዘንድ በብረት ሰንሰለት ለመታሰር ፈቀደ፤ መለው ዓለም እውነተኛ ነፃነት ይቀዳጅ ዘንድ በዚህ እጅግ በጣም ብርቱ ምሽግ ውስጥ እስረኛ መሆንን ተቀበለ። የምድር ሕዝቦች ዘላቂ ፍስሐን ይቀዳጁ፣ በደስታም የተሞሉ ይሆኑ ዘንደ የኃዘንን ጽዋ እስከ መጨረሻው ጠብታ ጨለጠ። ይህ ከሩኅሩኅ፣ ከእጅግ በጣም መሐሪው፤ ጌታችሁ ምህረት የተነሳ ነው። በአምላክ አንድነት አማኞች ሆይ፣ እናንተ ትከበሩ ዘንድ መዋረድን፣ እናንተ ትበለጽጉና ታብቡ ዘንድ ብዙ ከባድ መከራዎችን ተቀብለናል። እርሱን፤ መላውን ዓለም በአዲስ ይገነባ ዘንድ የመጣውን፣ እነዚያ ከአምላክ ጋር ራሳቸውን ያወዳደሩት፣ ከከተሞች እጅግ በጣም ባድማ በሆነው ከተማ ውስጥ እንዲኖር እንዴት እንዳስገደዱት ተመልከቱ!"*

## ባብ የባሃኦላህ መምጣት አዋጅ ነጋሪ

ባብ ከባሃኢ እምነት ማዕከላዊ ስብዕናዎች አንዱ ነው። የአምላክ ግልጸት ከመከሰቱ በፊት ስለእርሱ መምጣት የሚያወጅ ይመጣል። ለምሳሌ ክርስቶስ ራሱን ከመግለጹ በፊት መጥምቁ ዮሐንስ ለሕዝቡ የመሲሁ መምጫ መድረሱን ያውጅ ነበር። በተመሳሳይ ሁናቴ፣ ባሃኦላህን የሚያበስር መልዕክተኛ አምላክ ልኮ ነበር። ይህ ታላቅ መልዕክተኛ ባብ ይባላል።

ባብ ማለት በር ማለት ነው። ባብ በሰው ዘር ሕይወት ውስጥ የአዲስ ዘመን በር ነው። አዲስ የአምላክ ግልጸት ሊከሰት መሆኑን ለስድስት ዓመታት ሳያቋርጥ አስተማረ፤ መንገዱንም አዘጋጀ። ተስፋ የተገባለት አዲስ ዘመን ጉህ እየቀደደ መሆኑን ለህዝቡ አስተማረ። በቅርብ ጊዜ የሚገለጸውን የአምላክን ክስተት ለማወቅ ይችሉ ዘንደ ልቦቻቸውን ከምድራዊ ከንቱነት እንዲያፀዱ ለህዝቡ ጥሪ አቀረበ።

የባብን መልዕክት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ተቀበሉት። ትምህርቶቹንም መከተል ጀመሩ። ነገር ግን የኢራን መንግስትና ከፍተኛ ስልጣን የነበራቸው ካህናት በእርሱ ላይ ተነሱበት። ተከታዮቹም ጭቆና ደረሰባቸው፤ ብዙዎቹም ተገደሉ። ባብ በሰላሳ አንድ ዓመቱ በመንግስት ትዕዛዝ በ750 ወታደሮች ተኩስ አደባባይ ላይ ተሰቅሎ ተረሸነ። ሰማዕትነትንም ተቀበለ። ከሰማዕትነቱ በኋላ የባብ አስከሬን ከከተማው መግቢያ በሮች ውጪ ተጣለ። አካላዊ ቅሪቱ በተከታዮቹ ተወስዶ ከእምነቱ ጠላቶችም ለመደበቅ ከቦታ ወደ ቦታ ይዘዋወር ነበር። በመጨረሻም በቅድስት አገር (እስራኤል) ወደ ሚገኘው ቀርሜሎስ ተራራ ተወስዱ በመካነ መቃብር አረፈ።

## ባብ ከገለጻቸው ጸሎቶች መካከል

*“ከእግዚአብሔር በስተቀር ችግርን የሚያስወግድ አለ ወይ? በል፤ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው፣ እርሱ አምላክ ነው፣ ሁሉም አገልጋዮቹ ናቸው፤ ሁሉም በትዕዛዙ ይኖራሉ።”*

*“በል፣ እግዚአብሔር ሁሉን ነገሮች ከሁሉም በላይ ያረካል። በሰማይና በምድር ከእግዚአብሔር በስተቀር የሚያረካ የለም። በእውነቱ እርሱ በራሲ የሚያውቅ፣ ሕይወት የሚሰጥ፣ ምንም የማይሳነው ነው።”*

## የባሃኦላህ ቃል-ኪዳን

የባሃኢ ሃይማኖት አንዱ ዋነኛ እውነታ ቃል-ኪዳን ነው። በሁሉም ሌሎች

ሃይማኖቶች መልዕክተኛው ወይም ግልጸቱ ካረገ ወይም ከምድር ከተለየ በኋላ ተከታዮቹ በብዙ ነገሮች ላይ ሲጨቃጨቁ ኖረዋል። በዚህም ምክንያት ሃይማኖቶቻቸውን ወደ ብዙ ቅርንጫፎች ከፋፍለውታል።

አንድን መልዕክተኛ ወይም ነቢይ በሚከተሉ ምዕመናን ውስጥ የመከፋፈልና የመለያየት ዋነኛ ምክንያት ግለሰቦች ለመሪነት ያላቸው ከፍተኛ ፍላጐት ነው። በዚህም ምክንያት ብዙ ሃይማኖቶች ወደ ተለያዩ ቅርንጫፎች ተከፋፍለዋል፤ ምክንያቱም ክስተቱ ወይም መልዕክተኛው ስላስተማራቸው ወይንም ስለገለጻቸው ጽሑፎች የተለያየ አመለካከታቸውን የሚያስማማላቸው ስላልነበራቸው ነው።

በየሃይማኖቱ ጽኑ አማኞች መካከልም እንኳን ልዩነትና መቃቃር ይነሳል። ይህም ግልጽ በሆነ መንገድ ቃሉን ለመተርጐም ሥልጣን የተሰጠው በክስተቱ በራሱ የተሾመ መሪ ስላልነበረ ነው። ይህ ግጭትና የሀሳብ ልዩነትን አስነሳ። የእያንዳንዱ አተረጓጐምም አንዱን ሃይማኖት ከፋፍሎ የተለያዩ ቅርንጫፎችን ፈጠረ።

ባሃኦላህ የባሃኢ ሃይማኖትን ከእንደዚህ ዓይነት ክፍልፍሎሽ ጠብቆታል። ይህንንም ያደረገው ልዩ በሆነ ኃይል ማለትም በቃልኪዳኑ ኃይል እምነቱን በማስጠበቅ ነው። ይህም የቃልኪዳን ተቋም በመባል ይታወቃል።

ባሃኦላህ ከዚህች ዓለም ከመለየቱ በፊት በጽሑፍና ግልፅ በሆነ ቋንቋ ከእርሱ በኋላ ባሃኢዎች ወደ አብዱል-ባሃ በመዞርና የእርሱን መመሪያ መከተል እንዳለባቸው ገለጸ። በዚህ ቃልኪዳን የበኩር ልጁ የሆነውን አብዱልባሃን ብቸኛው የቃሉ ተርጓሚ፣ የቃልኪዳኑ ማዕከልና፣ የባሃኢ የሕይወት ተምሳሌት አድርጎ ሾመው።

አብዱልባሃን ያሳደገው ባሃኦላህ ራሱ ነበር። አብዱልባሃ ልጅ በነበረበት ጊዜ እንኳን የአባቱን የመልዕክተኛነት ደረጃና ክብር አውቆ ነበር። የአባቱን ስቃዮችም ተካፍሏል።

አብዱልባሃ የተወለደው ባብ እ.ኤ.አ 1844 ተልዕኮውን ባወጀበት ምሽት ነበር። እርሱ በምድር ላይ ለ77 ዓመታት ኖረ። ሕይወቱ በሥቃይ የተሞላ ነበር። ቢሆንም ግን እፊቱ የቀረቡትን ሁሉ በእጅግ በጣም ታላቅ ደስታና ፍስሐ ያጐናጽፋቸው ነበር።

ባሃኦላህ ካለፈ በኋላ የባሃኢ ማህበረሰብን የመምራት ኃላፊነት በአብዱልባሃ ትከሻ ላይ አረፈ። እርሱ እምነቱ በምስራቅና በምዕራብ እንዲሠራጭ በቀንና በማታ ይተጋ ነበር። በሁሉም ቦታ ላሉ ግለሰቦችና ቡድኖች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ መልዕክቶችን ጽፏል። የአባቱን ትምህርቶችም አብራርቷል።

አብዱልባሃ በባሃኦላህና በባብ ቅዱሳን ቃላት ላይ የሰጣቸው ትንታኔዎች የባሃኢ እምነት ጽሑፎች አስፈላጊ አካል ናቸው። በዓለም ዙሪያ ያሉ ባሃኢዎች የባሃኢነትን ሕይወት ለመኖርና አዲስ ሥልጣኔን ለመፍጠር በሚያደርጉት ጥረት አንድነታቸውን ጠብቀው መኖር የቻሉት የባሃኦላህ ቃልኪዳን ማዕከልና ተቋም በሆነው በአብዱልባሃ

ላይ በማተኮራቸው ነው።

አብዱልባሃ የማፍቀር ፍፁም ምሳሌ ነው። ፍትህ ማድረግ እንዳለብን፣ ለጋስ መሆን እንዳለብን፣ የሌሎችን ስህተት መመልከት እንደሌለብን፣ መንፈሳዊ ባህሪያትን ለማዳበር ጥረት ማድረግ እንዳለብ፣ ወዘተረፈ ያስታውሰናል። ከአብዱልባሃ ተምሳሌትነት ፍትህን፣ ልግስናንና ይቅርባይነትንና ብዙ መንፈሳዊ ባህሪያትን ማደበር እንደምንችል እንማራለን። ከሁሉም ይበልጥ ደግሞ በአብዱልባሃ ላይ በማተኮር ከባሃኦላህ ጋር የገባነውን ቃልኪዳን ሁል ጊዜ እናስታውሳለን። ይህም ቃልኪዳን የተከታዮቹ አንድነት እንዲናጋ ፈፅመን የማንፈቅድ መሆናችንንና እንደ አንድ ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ተዋህደን የሰው ልጅ አንድነት በጥብቅ እንዲመሠረት በጽናት ለመትጋት ቆርጠናል ማለት ነው።

አብዱል-ባሃም በተራው በቃለ-ኑዛዜውና በቃልኪዳኑ የእርሱን የቃልኪዳንነት ተቋም ወደ ከፍተኛው ደረጃ የሚያሻግር እንዲሆን የልጅ ልጁ የሆነውን ሾጊ ኤፌንዲን የባሃኢ እምነት ሞግዚት አድርጐ ሰየመው። ከአብዱል-ባሃ ከዚህ ዓለም መለየት በኋላም ሾጊ ኤፌንዲ የባሃኦላህን ትምህርቶች የመተርጐም ሥልጣን የተሰጠው ሆነ። የክስተቱን ቃላት በማብራራትና እምነቱንም በዓለም ላይ በጥብቅ በመመሥረት ቃልኪዳኑም የተቋምነት ከፍተኛ ደረጃውን እንዲይዝ፣ ማለትም ዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትህ የተባለውን የባሃኢ ከፍተኛ ተቋም እንዲቋቋም መሠረት በመጣል ለ36 ዓመታት አገልግሏል።

የእምነቱ ሞግዚት ሾጊ ኤፌንዲ ካረፈ ከአምስት ዓመት ተኩል በኋላ በዓለም ዙሪያ ያሉ ባሃኢዎች ዓለም አቀፍ ቤተ - ፍትህን በምርጫ አቋቋሙ። ይህ አካል እንደሚቋቋም ባሃኦላህ አስቀድሞ ገልጾ ነበር። ዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትህ፣ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ዙሪያ ለሚኖሩ ባሃኢዎች ሁሉ፣ በባሃኦላ ቅዱሳን ጽሑፎች ላይ የተመሰረቱ መመሪያዎችና ትንታኔዎች የሚመነጭበት ከፍተኛው የእምነቱ ተቋም ነው።

## የባሃኢ ሃይማኖት ጥቂት ሕግጋትና ትዕዛዛት

እያንዳንዱ የአምላክ መልዕክተኛ የሆነው ግልጸት የሰው ልጅ በትክክለኛው መንገድ እንዲመራ ሕግጋትንና ትዕዛዛትን ያመጣል። ከእነኚህ ሕግጋትና ትዕዛዛት አንዳንዶቹ ዘለዓለማዊ ናቸው። ሌሎች ደግሞ የሰው ልጅ ባደገና በተሻሻለ ቁጥር ይለወጣሉ።

እንደየወቅቱ የሰው ልጅ ህመምና አቅም የሚገለጹቱ የእግዚአብሔር ሕግጋት የ"አድርጉ" እና የ"አታድርጉ" ዝርዝሮች ብቻ ናቸው ብለን ማሰብ እንደሌለብን ባሃኦላህ ያስተምረናል።

ባሃኦላህ እንደሚነግረን የእርሱ ሕግጋቶች *"በአገሊጋዮቹ መካከል የፍቅራዊ እንክብካቤ ብርሃኖችና ለፍጡራኔ የምህረቴ ቁልፎች"* ናቸው። *"ትዕዛዛቴን ለውብቴ ፍቅር ስትሉ ጠብቁአቸው፤"* ብሎናል። ስለዚህ፣ የባሃኦላህ ሕግጋት እንደሌሎች

የእግዚአብሔር ሃይማኖቶች ሕግጋት ሁሉ፣ ለደህንነታችንና ለመዳናችን የተሰጡ የመንፈሳዊና የቁሳዊ ህመሞቻችን መፈወሻዎች፣ የመልአካዊ ተፈጥሮአችን መኮትኮቻና ማሳደጊያ የሕይወት ውሃዎች ናቸው።

**ፀሎት**

የሰው ልጅ በምደር ላይ ሲኖር በየቀኑ ምግብ መመገብ አለበት። ይህ ለሰው አካል አስፈላጊ ነው። ካልተመገብን ደክመን ቀስ በቀስ እስከ መሞት ልንደርስ እንችላለን። ስለዚህ መብላት ለምድራዊ ኑሮአችን መታዘዝ ያለብን ሕግ ነው። በተመሳሳይ መንገድ እንደ አካላችን ሁሉ ነፍሳችንም ሁልግዜ ምግብ ያስፈልጋታል።

ከባሃኦላህ ሕግጋት መካከል አንዱ በየቀኑ መፀለይ እንዳለብን ይነግረናል። ፀሎት ለመንፈሳዊ ዕድገታችን ምግብ ነው። ፀሎት ስናደርግ አምላክ ሕይወታችንንና ኑሮአችንን ይባርክልናል።

በባሃኢ ቅዱሳን መጽሐፍት ውስጥ፣ በባብ፣ በባሃኦላህና በአብዱልባሃ የተገለጹ ልብን የሚማርኩ ፀሎቶች ብዙ አሉ። እነኚህን ፀሎቶች ለብቻችን ወይንም በጋራ ሁነን መፀለይ እንችላለን። ከእነኚህ ፀሎቶች አንዳንዶቹ የተለየ ኃይል አላቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የግዴታ ፀሎቶች ናቸው።

ከግዴታ ፀሎቶች መካከል አንዱ የሆነውን አጭር ጸሎት ባሃኢዎች በየቀኑ በቀትርና በፀሐይ መጥለቅ (6፡00 – 12፡30) መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲፀልዩ ታዘዋል። ይህ ጸሎት የሚከተለው ነው፡-

> *“አምላኬ ሆይ፣ አንተን እንዳውቅና እንድሰግድልህ እንደፈጠርከኝ እመሰክራለሁ። በዚች ሰዓት የእኔን ደካማነትና ያንተን ኃያልነት፣ ይእኔን ምስኪንነትና ያንተን ሃብታምነት አረጋጋጣለሁ። ከአንተ፣ በአደጋ ጊዜ ረዳት ከምትሆነውና በገዛ ራስህ ከምትኖረው አምላክ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።”*

ፀሎት ከአምላክ ጋር መነጋገር ነው። የእውነተኛ አፍቃሪ ብርቱ ፍላጐት ከሚያፈቅረው ሰው አለመለየትና ከእርሱም ጋር ማውጋት እንደሆነ ሁሉ አንድ ሰውም ለአምላክ ላለው ፍቅር ምልክት ይሆን ዘንደ ከእሱ ጋር መነጋገር አለበት። በሌላ አገላለጽ በየቀኑ መፀለይ ይገባዋል። ስለዚህም፣ ይህና ሌሎች የግዴታ ጸሎቶች፣ የግዴታ ቢባሉም፣ ለእኛው ደህንነትና ከፈጣሪያችንም ጋር በየዕለቱ ለመነጋገር ባለን ጥልቅ እሾት የምናደርገው የፍቅር መገለጫ እንጂ ሳንወደው የምንገደድበት ጉዳይ አይደሉም።

## ሐሜት

ባሃኦላህ ከሐሜትና ከስም ማጥፋት እንድንቆጠብ እንደሕግ ደንግጐታል። ይህን ማጤን ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም አንድነት እንዳይኖረን ከሚያግደን እጅግ በጣም ታላላቅ ጠላቶች አንዱ ሐሜት ነው። የሚያሳዝነው ነገር የሌሎችን ሰዎች ስህተቶች በሌሉበት ማውራት በብዙ ሰዎች ዘንድ በቀላሉ ሊቀየር የማይችል ልማድ ሆኗል።

እያንዳንዱ ሰው በሌሎች ሰዎች ጉድለቶች ላይ ሲያተኩርና እነኚህ ጉድለቶች ተደጋግመው ሲነገሩና ሐሜት ሲሆኑ እየጐሉ ይሄዳሉ። አብዱልባሃ የዚህን ተቃራኒ እንድናደርግ ይነግረናል። አንድ ሰው ላይ አስር ጥሩ ባህሪያትና አንድ ጉድለት ብንመለከት በአሥሩ ላይ ማተኮር አለብን። እንዲያውም አንድ ሰው አስር መጥፎ ባህሪያትና አንድ ብቻ ጥሩ ባህሪ ቢኖረው በዚያ በአንድ ጥሩ ባህሪ ላይ ማተኮር እንዳለብን ያስተምረናል።

ባሃኦላህ እንዲህ ይላል፡-

*እርኩስ ነገር አትስማ። እርኩስ ነገርም አትመልከት። ራስህን አታዋርድ፤ እንዲሁም አትዘን፤ አታልቅስ። እርኩስ ነገር አትናገር፤ ባንተም ላይ ሲናገር እንዳትሰማ። የሌሎችን ስሕተት አታጉላ፤ የራስህ አይሎ እንዳይታይብህ። የማንንም ውርደት አትመኝ፤ የራስህ ወራድነት እንዳይገለጽብህ። እንግዲህ በነጻነትና በእርካታ፣ ይህንን ሟች አካል ጥለህ፣ ወደ ረቂቃ ገነት ተመልሰህ፣ በማይጠፋው መንግሥት ለዘለዓለም ትኖር ዘንድ፣ ከመቅጽበት ከሚያልፍ ጊዜ ያነሱትን የሕይወትህን ቀኖች፣ በአእምሮህ እንከን-አልባ፣ በልብህ ያልጎደፍህ፣ በሃሳብህ ንጹህ፣ በተፈጥሮህም የተቀደስክ ሆነህ ኑር።*

## አልኮል መጠጦች

አልኮል መጠጣት በዛሬው ጊዜ በዓለም ውስጥ ካሉት እጅግ በጣም ታላላቅ ማህበራዊ ችግሮች አንዱ ነው። አላስፈላጊ የሆነ ኃይልን ለመጠቀምና ጤናማ የሆነ የቤተሰብ ኑሮን ለማፍረስ ብዙ ጊዜ ምክንያት የሚሆነው አልኮል መጠጥ ነው።

አምላክ ከእንስሳዎች የሚለየን ልዩ ስጦታ ሰጥቶናል። ይህም ስጦታ የማገናዘብና የማሰብ ችሎታ ነው። አልኮል ስንጠጣ ይህን ችሎታችንን እንድናጣና እንደእንስሳ እንድንሆነ ያደርገናል። አልኮል መጠጣት ሰዎች የሚያሳፍሩ ሥራዎችን እንዲሠሩ ያደርጋቸዋል። ግን፣ የተፈጠርነው ክቡር ተደርገን በመሆኑ ይህ ለኛ የማይገባ ነው።

ባሃኦላህ እንዲህ ይላል፡-

*የመንፈስ ልጅ ሆይ!*
*ሃብታም አድርጌ ፈጠርኩህ፤ ለምን ራስህን ወደ ድህነት ታወርዳለህ? ክቡር*

*አደረግሁህ፤ ለምን ራስህን ታዋርዳለህ? ከዕውቀት ምንጭ ሕይወት ሰጠሁህ፤ ለምን ከእኔ በቀር ከሌላ የዕውቀት ብርሃን ትሻለህ? ከፍቅር አፈር ሠራሁህ፤ እንዴት ራስህን ከሌላ ጋር ታወዳጃለህ? ዓይንህን ወደ ራስህ መለስ አድርግ፤ በውስጥህ ኃያል፤ ኃይል የተመላሁና በገዛ ራሴ የምኖር ሆኜ ታገኘኝ ዘንድ።*

**ጾም**

የባሃኢ እምነት ጾም ለ19 ቀናት (ማለትም ለአንድ የባሃኢ ወር) የሚቆይ ነው። የጾሙም ሕግ ከፀሐይ መውጣት እስከ ፀሐይ መጥለቅ ምግብና መጠጥ ከመውሰድ መታቀብ ነው። የጾምን ዓላማ በተመለከተ አብዱልባሃ ሲያብራራ እንዲህ ይላል፡-

*“ጾም ከሥጋዊ ፍላጐት የመጠበቅ ምልክት ነው። ጾም ምሳሌና አስታዋሽ ነው። ይህም ማለት ሰው ከምግብ ፍላጐት እንደሚከለከል ሁሉ ከግላዊ ምኞትና ፍላጐትም መጠበቅ ይገባዋል ማለት ነው። የጾም ወቅት በመሠረቱ የማሰላሰልና የፀሎት፣ የመንፈሳዊ ተሃድሶና ለማኙ በውስጣዊ ሕይወቱ ውስጥ መሻሻል ለማሳየት የሚሞክርበት፣ በነፍሱ ውስጥ ያሉትን ድብቅ ኃይላት የሚያድስበትና የሚያነቃቃበት ወቅት ነው። ስለሆነም፣ አስፈላጊነቱና ምክንያቱ በባህሪው መንፈሳዊ ነው። ጾም፣ ከራስ ወዳድነትና ከእንስሳዊ ፍላጐቶች የመወገድ ምልክት ነው።”*

**ልጆችን ማስተማር**

ወላጆችና ህብረተሰብ ልጆችን የማስተማር ግዴታ አለባቸው። ይህ ከባሃኦላህ ትምህርቶችና ትዕዛዛት አንዱ ነው።

ከአብዱልባሃ ጽሑፎች የሚከተለውን እናገኛለን፡-

*“ስለዚህ የአምላክ ተወዳጆች ... ልጆቻቸውን ሕይወታቸውን በመስጠትና በሙሉ ልባቸው ማሰልጠንና ከፅድቅና ከፍፁምነት የትምህርት ገበታ ማስተማር አለባቸው። በዚህ ጉዳይ ቸልተኛ ወይንም ልል መሆን የለባቸውም፤ ውጤታማነት የጐደላቸው መሆን የለባቸውም። በእርግጥ አንድ ጨቅላ ሕፃን መሃይም ሆኖ እንዲያድግ ከማድረግ ይልቅ ጭራሹኑ ባይኖር ይሻለው ነበር። ምክንያቱም ያ ከፋት የማያውቅ ሕፃን በቀጣይ ሕይወቱ በአምላክ ፊት በኃላፊነት የሚያስጠይቁት፣ በሕዝቡ የሚያስወቅሱትና ተቀባይነት የሚያሳጡት ቁጥር የሌላቸው ጉድለቶች ያሰቃዩታልና። ይህ ምን ዓይነት የከፋ ኃጢያአት፣ ምን ዓይነት ግድፈትስ ነው! የአምላክ ተወዳጆች ...*

*የመጀመሪያው ኃላፊነት ... በተቻለ መንገድ ሁሉ ሁለቱንም ጾታዎች፣ ወንዶችንና ሴቶችን ለማስተማር መጣር አለባቸው፣ በመካከላቸው ምንም ዓይነት ልዩነት የለም። የሁለቱም ድንቁርና ያስወቅሳል።”*

## የባሃኢዎች ዓላማ

ባሃኢዎች የባሃኦላህ ተከታይ እንደመሆናቸው መጠን ዓላማቸውም ባሃኦላህ የተላከበትን መለኮታዊ ተልዕኮ ማራመድ ነው። የባሃኢ ሃይማኖት የጥሩ አስተሳሰቦች ጥርቅም ሳይሆን ራሱን የቻለ፣ በደንብ የተደራጀ ሥርዓት፣ ሕግና ዓላማ ያለው ሃይማኖት ነው። የባሃኢ እምነት ህይወትም መንገድም የሆነ፣ ለዚህ ዘመን የተገለጸ ፈቃደ-እግዚአብሔር ነው። የባሃኢ ሃይማኖት እምነት በተግባር የሚተረጎምበት በእውቀት ላይ የተመሠረተ ሕይወት ነው። ከላይ እንደተባለው፣ ዓላማውም የመላው የሰው ዘር አንድነትን መመስረት ነው። በህግዚአብሔር ፈቃድ ላይ የተመሠረተው ይህ ትጋት፣ ተስፋ የተሰጣት የእግዚአበር መንግስት በሰማይ እንደሆነች ሁሉ እንዲሁም በምድርም እንድትሆን ያስችላል።

በዚህ ሥራ ሶስት ተሳታፊዎች እንዳሉ የእምነቱ የአስተዳደር ከፍተኛ አካል የሆነው ተቋም ዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትሕ ይነግረናል። እያንዳንዱ ተሳታፊ በጣም ጠቃሚ ሚና ይጫወታል። እነዚህም ሦስት ተሳታፊዎች:-

1. ግለሰቡ
2. ማህበረሰቡ፣ እና
3. የእምነቱ ተቋማት ናቸው።

## ግለሰቡ

እያንዳንዱ/ዷ የባሃኦላህ ተከታይ በባሃኦላህ ቃልኪዳን መጽናት፣ በቀን ተቀን ሕይወቱ/ቷ በባሃኦላህ ትምህርቶች መሠረት መመራትና የሰውን ልጅ ለማገልገል ጥረት ማድረግ ይጠበቅበ/ባታል።

ባሃኦላህ ሕይወት በሞት እንደማያበቃ አስተምሯል። አማኞች ከአምላክ ጋር ያላቸው ግንኙነት ዘለዓለማዊ እንደሆነ በማመን ከሞት በኋላ ላለው የነፍስ ሕይወት የሚያስፈልጓቸውን መንፈሳዊ መንፈሳዊ ባህሪያት በእዚህ ምድራዊ ሕይወታቸው ማዳበር አለባቸው። የሰው ዘር አንድነትን መመሥረት በሃሳብ ብቻ ሊሳካ የማይችል በመሆኑ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ያላሰለሰ ተግባራዊ ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል።

## ማኅበረሰቡ

ሰው የተፈጠረው ብቻውን እንዲኖር አይደለም። በጋራ አብሮ ተባብሮ

በማኅበረሰብ ደረጃ እንዲኖር እንጂ። ስለሆነም የባሃኢ ማኅበራዊ ሕይወት ከባሃኢዎች የማንነትና የእምነት መገለጫዎች አንዱ ነው። ባሃኢዎች አዲስ መንፈሳዊ ሥልጣኔን ለመገንባት፣ ይህንን ዓላማ ከሚያራምዱ የየትኛውም እምነት ተከታዮች ጋር በኅብረትና በሕብር ይሰራሉ።

የመጀመሪያው የባሃኢ ማኅበረሰብ ደረጃ የአንድ መንደርን ወይንም ከተማን የሚያቅፍው የአካባቢ ባሃኢዎች ማህበረሰብ ይባላል። ባሃኢዎች፣ ከትንሹ እስከትልቁ፣ እርስ በእርስ መተጋገዝን፣ በፍቅርና በህብረት እየተመካከሩና እየተደጋገፉ አብሮ ማደግን፣ ለሚኖሩበት ማኅበረሰብ አወንታዊ ለውጥ ቅንነት የተሞላው አስተዋፅዖ ማበርከትን የሚማሩት በዚህ ደረጃ ነው። ከዚያም በመቀጠል በብሔራዊና በዓለም ዙሪያ  ባለው የባሃኢ ማህበረሰብ ውስጥ የእያንዳንዱ አካባቢ ማህበረሰብ የራሱን ሚና ይጫወታል፤ እንደዓለም ዓቀፍ ማኅበረሰብ አካልነቱም ከሌሎች ጋር በትብብር መንፈስ ይሠራል፤ ይማራል፤ ያድጋል። ይህ ዓለም አቀፍ የባሃኢ ማህበረሰብ ሳያቋርጥ እየተስፋፋና ከሁሉም ሃይማኖቶች፣ ዘሮችና ብሔሮች ሰዎችን እየሳበ ይገኛል። ሊወለድ ያለው የአዲሱ የዓለም ሥርዓት፣ የአንድነትና የፍቅር ዘመን፣ ጥንስሱ በዚህ በባሃኢ ማኅበረሰብ ውስጥ ይታያል።

## የእምነቱ ተቋማት

ባሃኦላህ አዲስ የአስተዳደር ሥርዓት ደንግጓል። ይህ ማለት ምን ዓይነት ተቋማት መመስረት እንዳለብን፣ እነዚህ ተቋማት እንዴት እንደሚሠሩና የሰው ልጅ እንዴት በእነርሱ መተዳደር እንዳለበት በዝርዝር ገልጾልናል ማለት ነው።

በእያንዳንዱ አገር በዓመት አንድ ጊዜ ባሃኢዎች ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔን እንዲሁም በእያንዳንዱ አካባቢ (ቀበሌ፣ ወረዳ፣ ከተማ) የአካባቢ መንፈሳዊ ጉባዔን ይመርጣሉ። የማህበረሰቡን ጉዳዮች የሚመራውና የግለሰብ አማኞችንም ደህንነት የሚጠብቀው የአካባብ መንፈሳዊ ጉባዔ ነው።

የአካባቢ መንፈሳዊ ጉባዔ 9 አባላት አሉት። አባላቱ የሚመረጡት በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉት ጐልማሳ አማኞች (ዕድሜያቸው 21 ዓመት ከዚያ በላይ) ነው። ምርጫው የፀሎት መንፈስ በሰፈነበት ሁኔታ ያለቅስቀሳ በሚስጥር ይደረጋል።

መንፈሳዊ ጉባዔዎች እጅግ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ናቸው።  በእነርሱ አማካይነት የግልና የአካባቢ ጉዳዮችን እንዴት ማስተዳደርና አዲሱን ሥርዓት እንዴት መመስረት እንደሚቻል እንማራለን።  ይህ አዲስ ሥርዓት የባሃኦላህ ዓለም አቀፍ ሥርዓት ተብሎ ይታወቃል።

የባሃኢዎች ከፍተኛው ተቋም ደግሞ ዓለም ዓቀፍ ቤተ-ፍትሕ ይባላል። ይህም ተቋም በየአምስት ዓመቱ በዓለም ላይ ባሉ የባሃኢ ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔዎች

አማካኝነት ይመረጣል።

**ባሃኢ መሆን እንዴት ይቻላል?**

ባሃኢ ለመሆን አስፈላጊ የሆነው ነገር ባሃኦላህ ለዚህ ዘመን የአምላክ ግልጸት ወይም መልዕክተኛ እንደሆነ በነፃነት መርምሮ ማረጋገጥ፣ ከዚያም የአምላክ ቃላትና መመሪያ በባሃኦላህ በኩል እንደተገለጹ መቀበልና ማመን ነው። አንድ ባሃኢ ባሃኦላህን ከተቀበለ በኋላ በንቃት ትምህርቶቹን በሕይወቱ ላይ ተግባራዊ ማድረግ መጀመርና በየዕለቱ ስለ ባሃኢ እምነት ያለውን እውቀት ለመጨመር መጣር፣ ስለእምነቱ ላልሰሙ ሰዎችም ማሳወቅ አለበት።

ለበለጠ መረጃ፡-

**ባሃኢ ማዕከል**
**ፖ.ሣ.ቁጥር፡** 102 **አዲስ አበባ**
**ስልክ፡** 0116181372
www.bahaiethiopia.org